

# የጣት አሻንጉሊት

## ተግባሮች

PUPPETalk™

PUppets to Play, Praise, Educate, and Talk®

እርስዎ የልጅዎ የመጀመሪያና እጅግ አስፈላጊ አስተማሪ ነዎት። ህጻናትን ማዋራት ለአንጎላቸው እድገት እጅግ አስፈላጊው መንገድ እንደሆነ እናውቃለን። የጣት አሻንጉሊት እርስዎን እና ሌሎች የቤተሰብዎ አባላትን ከልጅዎ ጋር እንድታወሩ ይረዳችኋል። ልጅዎን በሚመግቡበት፣ በሚያጥቡበትና በሚያጫውቱበት ወቅት ያዋሩት። ለልጅዎ ዳይፐሩን በሚቀይሩለት እና በመኪና ወንበር ላይ በሚያስቀምጡበት ወቅት ያዋሩት የፈጠራ ችሎታ ይኑርዎ እንዲሁም ያዝናኑት። እያንዳንዱ ልጅ የተለየ ስለሆነ የራስዎን ልዩነቶች ይጨምሩ እንዲሁም አዳዲስ ተግባሮችን ይፍጠሩ።

**አሻንጉሊትዎ አብሮዎት ባይሆንም እንኳ ሁልጊዜም ልጅዎን ማዋራትዎን መቀጠል እንዳለብዎት ያስታውሱ!**

01 **የጣት አሻንጉሊትዎን በስሙ** ይጥሩተት እና የሚያበረታታና ረጋ ያለ ድምጽ አብረውት ያሰሙ።

02 **ኩ፣ ምላስና ከንፈርዎን እያንቀሳቀሱ ትርጉም የማይሰጡ ድምጾች ያሰሙ።** ለመናገር ተራ ስትቀያየሩ ልጅዎ የሚያወጣቸውን ድምጾች ይኮርጁ ወይም ደግመው ያውጡ።

03 **አሻንጉሊትዎን ወደ ላይ እና ወደ ታች እና ወደ ጎንና ጎን በሚያንቀሳቅሱበት ወቅት የልጅዎን ስም ይጥሩ።** ልጅዎን እንቅስቃሴውን እንዲከተል ለማድረግ ይሞክሩ። አሻንጉሊትዎን እየሸፈኑና እየገለጡ **peek-a-boo**ን ይጫወቱ። ልጅዎን፡ “አሻንጉሊትህ የት ነው? እዚህ ጋር ነው! ጥሩ አድርገሀል፣ አሻንጉሊትህን አግኝተሀል!” ሊሉት ይችላሉ።

04 **ህጻናት ረጋ ብለው መንካት እና መልዕክት ማስተላለፍ ይወዳሉ።** ልጅዎን ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ብርድ ልብስ ወይም የወለል ምንጣፍ ላይ ያስቀምጡት። ክርኖቿን ሳይጫኑ በጣቶችዎ መካከል ያሽከርክሩ። መነካካትዎን ክብ ቅርጽ ያላቸው ተረከዞቿ ወዳሉበት ወደ እግር መዳፏ ድረስ ይቀጥሉ። ልጅዎ እያዋሯት ቆንጆ ልጅ እንደሆነችና የተለያዩ የአካል ክፍሎቿን በስም ይንገሯት። በእግር ጣቶቿ እያጫወቷት **This Little Piggy Went to Market** ዜማን ይጨምሩ።

05 **ከመጽሀፎች እና መጽሄቶች ውስጥ ስዕሎችን ተመልከቱ።** ያያችሁትን ነገር ስሙን ይንገሩት እና ያብራሩለት። ልጅዎ በተለይም ጥቁር እና ነጭ፣ ብሩህ ቀለሞችን እና ፓተርኖችን ማየት ሊወድ ይችላል።

06 **በቤታችሁ ዙሪያ እየዞራችሁ አስሱ።** የምታገኟቸውን የተለያዩ ነገሮች በስም እየጠሩ ይንገሩት። ቀለሞችን፣ ቁጥሮችን፣ መጠኖችን፣ ቅርጾችን እና ስሪቶችን ይግለጹለት።

07 **የተለያዩ ትእይንቶችን በመጠቀም ከቤት ውጭ ያሉ ነገሮችን ያስሱ።** ልጅዎን ሳሮችን፣ ቅጠሎችን፣ የዛፍ ቅርፊት እና ሌሎች ቁሶችን እንዲያይ፣ እንዲነካና እንዲያሸት ያድርጉት። የንፋስ ሽውታው እንዲሰማችሁ ያድርጉ፣ ወፎችን አዳምጡ እንዲሁም አበቦችን አሽትቱ። ልጅዎ በሚያጠናበትና በሚያስስበት ወቅት አሻንጉሊትዎ ስለ እነዚህ ነገሮች ማብራራት አለበት።

08 **ቀላል መጽሀፎችን ያንብቡለት።** የቁሶችን ስም ይንገሩት እና የስዕሎች ቀለሞችን፣ ቅርጾችን እና ሌሎች ዝርዝሮችን ይግለጹለት።

09 **ሙዚቃዎችን እየዘፈኑላት እንደ Twinkle Twinkle Little Star, Old MacDonald Had a Farm, the Hokey-Pokey**, የመሳሰሉ ዜማዎችን እና ሌሎችንም ይበሉላት! በልጅነትዎ ይወዱት የነበረ ሙዚቃ አለ? ልጅዎን ረጋ ብሎ የሚሄደውን ዜማ እንዲሰማት ለማድረግ አሻንጉሊትዎን በዝግታ የልጅዎን ሆድ መታ መታ እንዲያደርግ እና በሙዚቃው እንዲወዛወዝ ያድርጉ።

10 **በየመወዛወዣ ጊዜ ልጅዎን ጭንቅላቷን እንድትቆጣጠር ለማድረግ አስፈላጊ መንገድ ነው።** ደህንነቱ በተጠበቀና ዝርግ ወለል ላይ ልጅዎን መወዛወዣዋ ላይ ያድርጓት። ልጅዎን አዲስ አሻንጉሊት እንድትፈልግ እና እራሷን በመስታወት ውስጥ እንድታይ ለመርዳት አሻንጉሊትዎን ይጠቀሙ። ልጅዎን ጭንቅላቱን እንዲያንቀሳቅስና አሻንጉሊቱን እንዲፈልግ ለመርዳት አሻንጉሊቱን በልጅዎ ዙሪያ ያዟዙሩ።

E PUPPETalk@cuanschutz.edu W PUPPETalk.org

©2017 The Regents of the University of Colorado. All Rights Reserved.